15¾ ›mT qÜ_R 11
15th Year No. 11

ÆHR ÄR ሐምሌ 1 ቀን 2002 ›/M
Bahir Dar July 8 , 2010

**bxþT×eÃ ØÁ‰§êE ÁäK‰sþÃêE ¶pÜBlþK**
**yx¥‰ B¼¤‰êE KLL MKR b¤T**

# ZKr ÞG

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

bx¥‰ B¼¤‰êE KL§êE mNGST MKR b¤T «ÆqEnT ywÈ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ 1324
ÃNÇ êU BR 178.00
Unit price 178.00

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 174/2002 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የ2003 በጀት ዓመትን በጀት ለማፀደቅና

የበጀት አስተዳደሩን ለመወሰን

የወጣ አዋጅ

**Content**

**Proclamation No. 174/2010**

**A Proclamation Issued to provide for the Approval of the 2010/2011 Fiscal Year Budget and the Determination of the Budget Administration of the**

## አዋጅ ቁጥር 174/2002 ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

## የ2003 በጀት ዓመት በጀት ማፀደቂያና አስተዳደሩን መወሰኛ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሠ) መሠረት ክልሎች የራሣቸውን በጀት ለማጽደቅና ሥራ ላይ ለማዋል በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በ2003 የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት ለሚያከናውናቸው ሥራዎችና ለሚያበረክታቸው አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት ማጽደቅና በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 174 /2010

## The 2010/2011 Fiscal Year Budget Approval and Determination of its Administration of the Amhara National Regional State Proclamation

**WHEREAS**, it is found necessary to approve and implement the budgetary appropriations required for the activities to be done and services to be rendered in the 2010/2011 budget

year, pursuant to the power vested in States, under Article 52 sub article 2(e) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, to appropriate their own budget and implement same.



በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የፌደራሉን መንግሥትና የክልሎችን የጋራ ገቢ ክፍፍል እንዲሁም የፌደራሉ መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠውን ድጐማ በተመለከተ የፌደሬሽን ምክር ቤት የወሰነውንና የክልሉን የተለያዩ ታሣቢዎች መሠረት በማድረግ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የ 2003 በጀት ማወጅ በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና (10) ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

**WHEREAS**, it has become necessary to proclaim the 2010/2011 budget of the National Regional State in accordance with the decision of the House of Federation and various considerations of the Regional States concerning joint revenue appropriations of the Federal Government to the Regional States pursuant to Article 62 sub-article 7 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**NOW, THEREFORE,** the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Article 49 sub-article 3(1 and 10) of the Revised Constitution of National Region, hereby proclaims as follows.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ 2003 በጀት ዓመት በጀት ማፅደቂያና አስተዳደሩን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 174/2002 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as “The 2010/2011 Fiscal Year Budget Approval and Determination of its

### 2. ለ 2003 የበጀት ዓመት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የተመደበ አጠቃላይ በጀት

ከሐምሌ 1/2002 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2003 ዓ.ም ባለው የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፌደራል መንግሥት ድጐማና ከክልሉ ከሚገኘው ገቢ፦

Administration of the Amhara National Regional State Proclamation No. 174/2010/2011."

**2. <u>Total Budget Appropriated for the 2010/2011 Fiscal Year to Implement the Activities of the Amhara National Regional State</u>**

For the Fiscal Year commencing on the 8th of July, 2010 and ends on the 7th day of July 2011, from Federal Government Subsidy and Regional Revenue;



**I.** ገቢ..... 7,004,104,210

1. ከመንግሥት ግምጃ ቤት:-...6,709,839,240

ሀ.በክልሉ የሚሰበሰብ መደበኛ ገቢ:.1,208,877,335

- ከታክስ ገቢ:-.....980,067,911
- ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች:-....228,809,424

ለ. ከፌዴራል መንግሥት ድጐማ (የቀመር ጥቅል ድርሻ):-..... .....5,500,961,905

2. በክልሉ የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ:-..172,824,970

3. ከውጭ አገር ብድር:-.....9,350,000

4. ከውጭ አገር ዕርዳታ:-.....112,090,000

ጠቅላላ የክልሉ የዘመኑ የበጀት ጣሪያ ብር 7,004,104,210 (ሰባት ቢሊዮን አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አራት ሺህ ሁለት መቶ አስር ብር) ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ የተመለከተው በጀት ተመድቧል።

**I.** Revenue ..... ....7,004,104,210

1. From State Treasury..... 6,709,839,240

A. Regional State revenues..... .....1,208,877,335

- Tax Revenues..... 980,067,911
- Non Tax Revenues..... 228,809,424

B. Federal Government Subsidy (formula of total division) .....5,500,961,905

2. Regional Internal State Revenue... 172,824,970

3. Foreign Loan .....9,350,000

**II.** ወጭ .....7,004,104,210

ሀ. ከመንግሥት ግምጃ ቤት:-..6,709,839,240

1. ለቢሮዎች መደበኛና ካፒታል ሥራዎች:-.....1,585,417,335
   - መደበኛ:-.....905,000,000
   - ካፒታል:-.....680,417,335

4. Foreign Assistance.....112,090,000

Total Ceiling of the Regional State Budget Birr 7,004,104,210 (Seven Billion, Four Million, One Hundred Four Thousand, Two Hundred Ten Birr) is hereby appropriated for the activities and services set forth in the schedule hereto.

**II.** Expenditure ..... 7,004,104,210

A. From State treasury**.....** 6,709,839,240

1. For the Bureaux Recurrent and capital activities ..... 1,585,417,335
   - Recurrent ..... 905,000,000
   - Capital ..... 680,417,335



2. ለወረዳዎች:-.....3,801,921,905
   - ለገጠር ወረዳዎች፥.....2,619,138,414
   - ለከተማ አስተዳደር ፥-.....400,310,166
   - ለብሔረሰብ ምክር ቤቶች (ወረዳዎችን ጨምሮ)፥-.....485,651,421
   - ለከተሞች ልማት ፈንድ (ለ 23 ነባር ከተማ አስተዳደሮች ልዩ ድጎማ)፥-.....200,000,000
   - ለከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

2. For Woredas..... 3,801,921,905
   - For Rural Woredas ..... 2,619,138,414
   - For City Administrations.....400,310,166
   - For the Nationality Councils (including Woredas) .....

መደበኛ ወጪ.....59,321,905

- ለኢንዱስትሪ መንደር ምስረታ የካሳ ክፍያ፡-
  .....30,000,000
- አዲስ ለሚዋቀሩ ወረዳ አስተዳደሮች ስራ ማስጀመሪያ ፡-
  .....7,500,000

3. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
   የማሠልጠኛ ማሽን ግዥ:-.....127,500,000
4. ለከፍተኛ መስኖ ግንባታ:-.....200,000,000
5. ለተዘዋዋሪ ፈንድ (በክልል ደረጃ ለወረዳዎች ለሚገዙ ዕቃዎች):-...20,000,000
6. ለወረዳዎች ተሽከርካሪ ግዥ:-.... 100,000,000
7. ለገጠር መንገዶች ግንባታ:-..... 120,000,000
8. ለገጠር መጠጥ ውኃ ግንባታ:-.....100,000,000
9. ለገጠር መንገድ ባለሥልጣን
   ማሽነሪ ግዥ:-.....100,000,000
10. ለ 30 ገጠር ሆስፒታሎች ንባታ:.....200,000,000
11. ለ 6 ኮሌጆች ግንባታ:-.....75,000,000
12. የክልል አቅም ግንባታ
    ማስፈፀሚያ:-.....70,000,000
13. መጠባበቂያ በጀት:-.....210,000,000

485,651,421

- For Cities Development Fund (For 23 existed City Administrations special subsidy).....200,000,000
- For Preparatory Schools Recurrent Expenditure .....
  .....59,321,905
- Compensation Payment For the Industry zone development ..... 30,000,000
- For Starting works of the new Woreda's Administrations.....
  ....7,500,000

3. For Purchasing Training Machine of Technic schools ..... 127,500,000
4. For the Building of Higher Irrigation
   .....200,000,000
5. For Revolving Fund (for Materials which will be purchased for Woredas at Regional Level).....
   20,000,000
6. Purchasing vehicles for woredas....
   100,000,000
7. For Rural Roads bulding .....
   120,000,000
8. For Rural potable water bulding
   .....100,000,000
9. Purchase of Machinery for Rural Roads Authority ..... 100,000,000
10. For 30 Rrural Hospitals Building ...
    200,000,000
11. For 6 Colleges Building .....
    75,000,000

12. For the Implementation of Regional Capacity Building…… 70,000,000

13. For Reserve Budget …… 210,000,000



ለ. የውስጥ ገቢ ……**.. 172,824,970**

1. ለትምህርት ቢሮ(ለመምህራን ትምህርት ኮሌጅ):-……41,352,065

2. ለጤና ቢሮ(ለሆስፒታሎች):-……25,112,727

3. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስፋፊያ ኤጀንሲ:-……102,750,000

4. ለማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን:- ……3,610,178

ሐ.ከውጭ አገር ብድር ……9,350,000

- ለቢሮዎች:-……1,221,855
- ለወረዳዎች:-……8,128,145

መ. ከውጭ አገር እርዳታ…… 112,090,000

- ለቢሮዎች:-……24,656,226
- ለወረዳዎች:-……87,433,774

## ክፍል ሁለት
## ስለበጀት አስተዳደር

### 3. በጀቱ ስለሚተዳደርበት ሕግ

የክልሉ የበጀት አስተዳደር የሚመራው በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 እና በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 6/1990 እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በወጡ መመሪያዎችና የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ይሆናል።

B. **Internal Revenue..**…… **172,824,970**

1. For Education Bureau (for Teachers Educational College)…… 41,352,065

2. For Health Bureau (for Hospitals)…… 25,112,727

3. For Technical and Vocational Education Training Progressive Agency…….102,750,000

4. For Prison Administration Commission…… ….3,610,178

C. From Foreign Country Loan ……9,350,000

- For the Bureaux …… 1,221,855
- For the Woredas …… 8,128,145

D. From Foreign Country Assistance…… 112,090,000

- For the Bureaux

……..24,656,226

- For the Woredas……..87,433,774

## PART TWO
## BUDGET ADMINISTRATION

### 3. The Law of Budget Administration

The Budget Administration of the Regional State shall be directed pursuant to the Amhara National Regional State Finance Administration Proclamation No. 18/1997 and the Regional State Finance Regulation No. 6/1998 as well as directives and working procedures issued by the Bureau of Finance and Economic Development.



### 4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስለሚኖረው በጀት የማስተዳደር ሥልጣን

በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 23 ንውስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለአዲስ ወይም በበጀት ዓመቱ ለተፈቀዱ ለካፒታልም ይሁን ለመደበኛ ሥራዎች ከውጭ ብድር፣ ከዕርዳታ ወይም ከሀገር ውስጥ ብድር፣ ዕርዳታ ወይም ከሌላ ምንጭ ተጨማሪ ገቢ ሲገኝ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እየተወሰነ በሥራ ላይ እንዲውል ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሲሰበሰብ ለበጀት ዓመቱ በተጨማሪ በጀትነት እንዲፀድቅ ይደረጋል።

### 4. Budget Administration Power of the Council of the Regional Government

Without prejudice to the provision of sub-article 1 of Article 23 of the Amhara National Regional State Budget Administration Proclamation (as amended) No. 18/1997, the Council of the Regional Government shall decide and implement when additional income is gained from foreign loan,from aid or domestic loan aid, or from other sources for new activities unspecified in the proclamation hereof, or for those capital and recurrent activities

### 5. የብሔራዊ ክልሉ አስፈፃሚ አካላት በጀት የማስተዳደር ሥልጣን

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለየሥራ ክፍሎቻቸውና ፕሮጀክቶቻቸው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የማስተዳደር

ሥልጣን አላቸው።

2. በዞን ደረጃ ምክር ቤት ያላቸው አስተዳደሮች ለዞንና ወረዳ በዚህ የበጀት አዋጅ የተሰጣቸውን የበጀት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን አላቸው።
3. የወረዳ አስተዳደር በዚህ የበጀት አዋጅ የተሰጠውን የበጀት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ስልጣን አለው።

approved in the budget year, and the Regional Council shall thereby approve same as a supplementary budget when holding its session.

## 5. Budget Administration Power of the Executive Organs of the National Region

1. The Heads, of the Government Offices of the Amhara National Regional State, are hereby authorized to administer the budget appropriated, pursuant to this proclamation, for the services of their respective departments and projects.
2. Administrations having a council at the Zonal level are here by fully authorized to administer the budget based on the budget ceiling allocated to the Zone and the Woredas by this proclamation.
3. The Woreda administration is hereby fully authorized to administer the budget based on the budget ceiling allocated to it by this proclamation



4. በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ ከተፈቀደላቸው በጀት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ መሠረት ታዟል።

## 6. የወረዳዎች ገቢን የማስተዳደር ሥልጣን

በሃብት ክፍፍል ወቅት በቀመር ለወረዳዎች የደረሣቸው የመንግሥት

4. Where Executive Organs of all level require disbursement from the budget allocated to them, the Head of Finance and Economic Development Bureau is hereby ordered, pursuant to this proclamation, to disburse same from the National Regional State

ግምጃ ቤት ጥቅል በጀት በወረዳ የሚሰበሰበውን ገቢ እና ከክልሉ መንግሥት የሚላከውን ድጐማ ያጠቃልላል። ወረዳዎች ይሰበስቡታል ተብሎ ከሚታሰበው የገቢ ዕቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ ይኸው በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ተወስኖ በተጨማሪ በጀትነት እንዲታወጅ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እየቀረበ በክልሉ ምክር ቤት አማካኝነት የሚፀድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው እስኪፈፀም ድረስ ግን ገቢውን በሥራ ላይ የማዋል ስልጣን ይኖራቸዋል።

7. <u>የበጀት ዝውውር ስልጣን</u>

ከዚህ በታች ለተመለከቱት አካላት በዚህ አዋጅ መሠረት የበጀት ዝውውር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል።

**1/** የ<u>አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ</u>

ሀ.ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ የመደበኛ በጀት ወደሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አስቀድሞ ለተፈቀደ ወይም ላልተፈቀደ መደበኛ ወይም ካፒታል በጀት፤

Revenues and other sources.

## 6. <u>Revenue Administration Power of the Woredas</u>

The State Treasury Total Budget appropriated for the Woredas during budget allocation shall include the revenue collected in the woreda and the subsidy provided by the Regional Government. Where woredas collect revenue exceeding to their collection plan, the woredas shall have power to appropriate the revenue and implement same up on the decision of woreda administration council and thereby submit same to the Bureau of Finance and Economic Development without prejudice to its approval by the Regional Council, to be proclaimed as additional budget.

## 7. <u>Power of Budget Transfer</u>

The power to transfer Budget is vested with the following bodies, pursuant to this proclamation indicated herein under.

**1/ <u>The Amhara National Regional State Finance and Economic Development Bureau shall transfer Budget:</u>**

A. From appropriations made for recurrent Budget of a Government Office to Previously appropriated or non appropriated Recurrent or Capial Budget of another Government Office;

ለ.ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ የካፒታል በጀት ወደሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አስቀድሞ ለተፈቀደ ወይም ላልተፈቀደ ካፒታል በጀት፤

ሐ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ከመደበኛ በጀት ወደ ተፈቀደ ካፒታል ፕሮጀክት፤

መ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ከአንድ ካፒታል ፕሮጀክት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ ካፒታል ፕሮጀክት፤

ሠ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ከአንድ የሥራ ክፍል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል የማዛወር፤

ረ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፤

ሰ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር፤ እና

ሸ.በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ስልጣን አለው።

**2/** <u>የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቶች</u>

ሀ. አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማዛወር፣

B. From appropriations made for capaital Budget of a Government Office to previously appropriated or non appropriated Capital Budget of another Government Office;

C. From Recurrent Budget to appropriated capital project upon the request of a Government Office at the Regional Level;

D. From One Capital project to another previously appropriated capital project upon the request of a Government Office at the Regional level;

E. From one Operational Department to another Operational Department upon the request of a Government Office at the Regional level;

F. From appropriations made for Salary and Allowance to Operational expenditure upon the request of a Government Office at the Regional level;

G. From One item of Expenditure to another item of Expenditure within one Operational Department upon the request of a Government Office at the Regional level; and

H. From one item of Expenditure to another item of Expenditure within a project upon the request of a Government Office at the Regional

level.

**2/ <u>Administrative Councils of Nationality Shall have the Power to:</u>**

A. Transfer from one Government Office to another Governement Office where the Administration deems necessary;



ለ. የአስተድር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መደበኛ በጀት በጀቱ ወደ ተያዘለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ካፒታል በጀት የማዛወር፣

ሐ. የአስተዳድር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ካፒታል በጀት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ/ያልተፈቀደ ካፒታል በጀት የማዛወር፣

መ. የአስተዳደር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በወረዳ የተያዘን የመደበኛና የካፒታል በጀት በጀቱ በተፈቀደለት ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የጽሑፍ ስምምነት መሠረት ወደ ዞኑ ወይም ወደ ሌላ ወረዳ የማዛወር ስልጣን አለው።

**3/ <u>የብሔረሰብ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ</u>**

ሀ. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት /ቅርንጫፍ ሲጠይቅ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ከአንድ የሥራ ክፍል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል የማዛወር፣

ለ. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ሲጠይቅ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ የተፈቀደ ፕሮጀክት የማዛወር፣

B. Transfer from Recurrent Budget of the Government Office to a Governement Office from which the budget is allocated, or to the Capital Budget of another Government Office where the Administrative Council deems necessary,

C. Transfer from Capital Budget of the Governement Office to another previously appropriated/ non-appropriated capital Budget where the Administrative Council deems necessary,

D. Transfer the Recurrent and Capital Budget allocated for the Woreda to the Zone or another Woreda in accordance with a written agreement made by the Woreda Administrative Council for which the Budget is appropriated where the Administrative Council deems necessary.

**3/ <u>Finance and Economic Development Department of the Nationality Administration shall have the Power to:</u>**

A. Transfer from One Operational Department to another Operational Department under the same Governement Office upon the request of a government office /branch at the zonal level,

B. Transfer from one project to another appropriated project under the same Governemnt Office upon the request of a Governement Office Branch at the Zonal level,



ሐ. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለአንድ የሥራ ክፍል ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ የማዛወር፣

መ. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር፣ እና

ሠ. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ሥልጣን አለው።

**4/ <u>የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት</u>**

ሀ. የወረዳ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በተፈቀደ የካፒታል በጀት ውስጥ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት፣

ለ. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመደበኛ በጀት ወደ ካፒታል ፕሮጀክት የማዛወር፣

ሐ. የወረዳ አስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለአንድ

C. Transfer from salaries and allowances appropriated for one Operational Department to Operational Expenditure upon the request of a Governement Office at the Zonal level,

D. Transfer from one item of Expenditure to another item of expenditure within the same operational department upon the request of a Governemt Office at the Zonal level, and

E. Transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same

የሥራ ክፍል ከተፈቀደ መደበኛና ካፒታል በጀት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ /ያልተፈቀደ መደበኛና ካፒታል ፕሮጀክት የማዛወር፣

መ.የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማዛወር ስልጣን አለው።

project where a Government Office at the Zone level requests.

**4/ The Woreda Administrative Council shall have the power to:**

A. Transfer from one project to another project within appropriated capital Budget where the Woreda Governemnt Office requests,
B. Transfer from Recurrent Budget to Capital Project where the Woreda Administrative Council deems necessary,
C. Transefer from Recurrent and capital Budget appropriated for one operational department to another previously appropriated/non appropriated Recurrent and Capital Project where the Woreda Administrative Council deems necessary,
D. Transfer budget from a Government Office to another Government Office where the Woreda Administrative Council deems necessary.



**5/** የወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ዋና ጽህፈት ቤት

ሀ. በወረዳ ያለ የመንግሥት መስሪያ ቤት ሲጠይቅ ለአንድ የሥራ ክፍል ከተያዘው በጀት ወደ ሌላ የሥራ ክፍል፣

**5/ Finance and Economic Developmnet Main Office of the Woreda shall have the Powe to:**

ለ. በወረዳ ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ የማዛወር፣

ሐ. በወረዳ ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር፣

መ. በወረዳ ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ሥልጣን አለው።

**8.** <u>የከተሞች በጀት የማስተዳደር ስልጣን</u>

1. **በዚህ አዋጅ አንቀጽ ll/ሀ/ 2 ስር የበጀት ድጋፍ የተደረገላቸው የከተማ አስተዳደሮች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 በአንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በበጀት ዓመቱ የተፈቀደና ወጪ ሳይደረግ ወይም ሥራ ላይ ሳይውል የቀረ ሂሳብ ሁሉ ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የትሬዠሪ ሂሳብ ፈሰስ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም ስለአጠቃቀሙ በየደረጃው ለሚገኙት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤቶች ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።**

A. Transfer from Budget appropriated for one Operational Department to another Operational Department upon the request of a Government Office at the Woreda level,

B. Transfer from appropriations of the Recurrent Budget allocated for salarly and allowance to operations Expenditure upon the request of a Government Office at the Woreda level,

C. Transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same project upon the request of a Government Office at the Woreda level,

D. Transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same Operational Departmenet upon the request of a Governement Office at the Woreda level.

8. **<u>Budget Administration Power of Cities</u>**

1. Subsidized City Administrations under Article II(A)2 of this proclamation required to send pursuant to Article 28 sub-article 1 of the Amhara National Regional State Finance Administration Proclamation No. 18/1997, those appropriated but unused or unimplemented accounts within the Fiscal year, to treasurey account of Finance and Economic

Development Bureau, instead of implementing same for operations. In addition, should submit monthly account report to Finance and Economic Development Offices at all level.



2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ll/ሀ/ 2 ስር ልዩ ድጎማ የተደረገላቸው የከተማ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ልዩ ድጐማ ለተፈቀደው ተግባር ብቻ የማዋል ግዴታ አለባቸው። በጀቱን በአግባቡ ሥራ ላይ ያዋሉት ስለመሆኑም የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የመቆጣጠር ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ll/ሀ/ 2 ለከተሞች ልማት ፈንድ ከተመደበው ብር 200,000,000 ሚሊዮን በጀት ውስጥ ለባህር ዳር፣ ጐንደር፣ ደሴ እና ኮምቦልቻ ከተሞች ለእያንዳንዳቸው ከሚደርሳቸው በጀት የከተሞች መሠረተ ልማት ኘሮጀክት መቀናጀ የሚታሰብ ሆኖ ይህም ክልሉ የሚያዋጣው የመቀናጀ በጀት ይሆናል።

**9.** <u>የከተማ አስተዳደሮች ገቢን የማስተዳደር ሥልጣን</u>

1. በታሪፍ ክፍፍል ወቅት ከጐንደር፣ ባህር ዳር እና ደሴ የከተማ አስተዳደሮች እና በ 2002 በጀት ዓመት ራሳቸውን ችለው ከተደራጁት 15 የከተማ አስተዳደሮች ውጪ ላሉት 20 የከተማ አስተዳደሮች በቀመር የደረሣቸው የመንግሥት ግምጃ ቤት ጥቅል በጀት በከተማ የሚሰበሰበውን መደበኛ ገቢ እና ከክልሉ መንግሥት የሚላከውን ድጐማ የሚያጠቃልል ይሆናል።

2. Those City Administrations for which special subsidy is made for them by Article II/A/2 of this proclamation shall implement same only for the appropriated Operations. So, the Regional Finance and Economic Development Bureau is given the power by this proclamation to control the proper implementation of the Budget.

3. In accordance with Article II/A/2 of this proclamation, the allocated 200 Milion Birr fund for cities development of Bahir Dar, Gondar, Dessie, and Kombolcha's shared budget the cities infrastructure project shall be calculated from each share and shall be matching fund of the Region.

## 9. <u>Income Administration Power of the City Administrations</u>

1. During resource sharing with the exception of Gondar, Bahir Dar and

Dessie and the other Fifteen City Administrations organized in 2002 E.C budget year, the Twenty City administrations get state treasury sum budget include the recurrent budget gathering with the city and the subsidized budget from the Regional Government.



2. ከተሞች ከታሰበዉ የገቢ ዕቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ ይኸዉ በየከተማው ምክር ቤት ተወስኖ በተጨማሪ በጀትነት እንዲታወጅ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እየቀረበ በክልሉ ምክር ቤት የሚፀድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው እስኪፈፀም ድረስ ገቢውን በሥራ ላይ የማዋል ስልጣን ይኖራቸዋል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የጐንደር፣ የባህር ዳር እና የደሴ ከተማ አስተዳደሮች እና በ 2002 በጀት ዓመት ራሳቸውን ችለው የተደራጁት 15 የከተማ አስተዳደሮች የሚሰበስቡትን መደበኛ ገቢ ለክልሉ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ **የትሬዠሪ ሂሳብ** ፈሰስ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## 10. የውስጥ ገቢ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/ዘ/ለ/ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የውስጥ ገቢ የተመደበላቸው መስሪያ ቤቶች የበጀት አጠቃቀም በሥራ ላይ ያሉትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

2. መሥሪያቤቶች ይሰበስባሉ ተብሎ ከሚታሰበው የውስጥ ገቢ ዕቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ በሚመለከተው አካል ተወስኖ በተጨማሪ በጀትነት እንዲታወጅ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እየቀረበ በክልሉ ምክር ቤት የሚፀድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ይኸው እስኪፈፀም ድረስ የውስጥ ገቢን

2. Without prejudice when the cities accumulate revenue more than the plan being decided with the city administrative council to be proclaimed as additional budget shall sent to the Finance and Economic Development Bureau issued with the regional council; however, still proclaimed the city administrations have power to implemnent the revenue.

3. Without prejudice sub-article 1 and 2 of this Article provisions, the accumulated recurrent income by Gondar, Bahir Dar, and Dessie and the fifteen city administrations organized in 2002 E.C Fiscal year shall send to treasury account of Finance and Economic Development Bureau.

## 10. Internal Revenue

በሥራ ላይ የማዋል ስልጣን ይኖራቸዋል።

1. In accordance with Article 2/II/B sub number 1 up to 4 of this proclamation, sectors use of budget allocated with internal revenue shall be based on applicable proclamations, Regulations and Directives.

2. Without prejudice when those sectors accumulate internal revenue more than the plan being decided with the concerned body to be proclaimed as additional budget shall be sent to the finance and Economci Development Bureau issued with the Regional council, however, still proclaimed those sectors have power to implement the internal revenue.



3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ለ/ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የውስጥ ገቢ የተመደበላቸው መስሪያ ቤቶች የበጀት አጠቃቀምን አስመልክቶ የድርጊት መርሃ ግብር እና አፈፃፀም በማዘጋጀት ለክልሉ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

3. In accordance with Article 2/II/B sub number 1 up to 4 of this proclamation, sectors allocated with internal revenue, concerning to budget usage by preparing checklist and its implementation should submit report to Finance and Economic Development Bureau and Offices at all level.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART THREE

**11.** ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**12.** መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የሚረዱትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**13** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 1 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሐምሌ **1** ቀን **2002** ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

**11. Inapplicable Laws**

Any law, regulation or directives inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters stated in this proclamation.

**12. Power to Issue Directives**

The Regional Finance and Economic Development Bureau may issue detailed directives necessary for the implementation of this proclamation.

**13. Effective Date**

This proclamation Shall come into force as of the 8th day of July 2010.

**Done at Bahir Dar,**
**This 8th day of July, 2010.**
**Ayalew Gobezie**
**President of the Amhara National Regional State**